የኢትዮጵያውያን ማኅበር
በስዊዘርላንድ

ASSOCIATION DES
ETHIOPIENS EN SUISSE

ኢማስ - AES
Case postale (P.O.Box) 2208 – 1211 Genève 2
aes@cyberethiopia.com

# <u>የሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ</u>

## የህዝባችን ድመጽ ይከበር! አፈናና ግድያው ይቁም!

በግንቦት/97 ምርጫ በነቂስ ወጥቶ የተሳተፈው ህዝባችን የወያኔ/ኢህአዴግ የግፍ አገዛዝ ያንገፈገፈው በመሆኑ እንዲወገድለት እንደሚሻ በማያሻማ ሁኔታ ገልጿል። ይህም ሀቅ በአለም አቀፍ ታዛቢዎች ጭምር ተረጋግጧል። የአቶ መለስ አመራርና ጥቂት ጭፍሮቹ የህዝባችንን ውሳኔ እንደማይቀበሉና የግፍ አገዛዙን በጉልበትና በማን አለብኝነት በህዝባች ንላይ ጭነው ለመቀጠል ያላቸውን ቅዠት በየእለቱ በሚያካሂዱት አፈናና ግድያ እያሳዩ ይገኛሉ።

ዛሬ ያለንበት ሁኔታ ህዝባችን የወያኔን የግፍ አገዛዝ ተሸክሞ መቀጠል የማችልበት ብቻ ሳይሆን ይህንን በዴሞክራሲያዊ እና በሰላማዊ መንገድ በግልጽና በቁርጠኝነት እየታገለ የመለስ አገዛዝ የሚያከትምበትን እለት እየቆጠረ ይገኛል።

ይህንን ዴሞክራሲያዊ፣ ሰላማዊና ህጋዊ የህዝብ ውሳኔ ወደጎን በመግፋት የስልጣን ጥማቱን ለማርካት ህገወጥ የጉልበት መንግስት ለማቋቋም እየተጣደፈ ያለው የመለስ ዜናዊ ቡድን አፈናውንና ግድያውን በመላው ሀገራችን አስፋፍቶ ሀገራችንን እና ህዝባችንን ወደ አላስፈላጊ ውጥረት ውስጥ በመክተት ላይ ይገኛል።

ታላቁ ህዝባችን በተለመደው ጨዋነት የወያኔን የጉልበት እርምጃ በሰላማዊ ሰልፍ ለመቃወ ም ለኦክቶበር 2 ቀን 2005 ዓ.ም ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ በመላው ሀገሪቱ ለማድረግ ማቃዱ የሚታወስ ነው። የህዝብ ቁጣ ያርበደበደው የመለስ ዜናዊ ግፈኛ አገዛዝ ይህ ሰላማዊ ሰል ፍ እንዳይደረግ አግዷል።

የወያኔ አገዛዝ የህዝባችንን ሰብአዊና ህገ መንግስታዊ መብት በመርገጥ የህዝቡን ሰላማዊ ትግል ለማፈን በጋዜጣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን በማሸበርና በማስፈራራት ላይ በመሆኑ ውጥረቱ እየተባባሰ ይገኛል። አቶ መለስና ጭፍሮቹ በጉልበት በስልጣን ለመቆየት በሚያደርጉት አጉል መፍጨርጨር ምክንያት ለሚደርሰው ችግርና ጉዳት ሙሉ በሙሉ ተጠያቂ እንደሚሆኑ ግልጽ  ሊሆን ይገባል።

በዚህ አስጨናቂና ወሳኝ ወቅት ከህዝባችን ጎን በመቆም የህዝባችንን ድምጽ እና ብሎም ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብት እንዲከበር መጠየቅ የሁሉም ኢትዮጵያዊ የዜግነት ግዴታ ነው።

በመሆኑም በመላው ሀገራችን የሚገኝ ህዝባችን በአንድ ላይ በመነሳት መብቱ እና ድምጹ እንዲከበር የሰላማዊ ሰልፍና የታቃውሞ መብቱ መታፈኑን በማውገዝ እኛ በስዊዘርላንድ የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን የህዝባችንን ጩኸት ለአለም ህብረተሰብ እንድናሰተጋባና ወያኔ ኢህአዴግ በህዝባችን ላይ እየወሰዳቸው የሚገኘውን ህገወጥ ኢ-ሰብአዊ የአፈና እርምጃዎች እንድናጋልጥ ጥሪያችን እናቀርባለን።

በስዊዘርላንድ የሰብአዊ መብት እና የምርጫ 97 ኮሚቴ

የሰላማዊ ሰልፍ መጀመሪያ ቦታ
Place des Nations /GENEVE / የተባበሩት መንግስታ ጽ. ቤት ፊት ለፊት/
እሁድ 2 October / ከቀኑ14.00 ሰአት ጀምሮ / ጄኔቭ